ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ.ም

# በድጋሚ የወጣ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉትን እና ዩኒቨርሲቲውን በምክትል ፕሬዚዳንትነት ለመምራት ፍላጎቱና ብቃቱ ያላቸውን የዩኒቨርሲቲውን አካዳሚክ ስታፍ አባላትን ወይም ከሌሎች ከታወቁ ዩኒቨርሲቲዎች የሚመጡ አመልካቾችን አወዳድሮ የላቀ ውጤት ያመጣውን/ችውን ተወዳዳሪ ለመመደብ ይፈልጋል፡፡

## 1. ስለተቋሙ አጭር መግለጫ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ፈር ቀዳጅ እና በአፍሪካም ስመ ጥር ከሚባሉት ዩኒቨርሲቲዎች መካከል የሚመደብ፣ ከ50 ሺ.ህ በላይ ተማሪዎችን ከ7 ሺ.ህ በላይ የሚሆኑ መምህራንን፣ ተመራማሪዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በመያዝ በርካታ የድህረ-ምረቃና የቅድመ-ምረቃ ፕሮግራሞችን የሚያካሂድ፣ ትላልቅ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸውን የምርምር ስራዎችን የሚያከናውን እንዲሁም ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚሰጥ አንጋፋና ግዙፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡

## 2. የስራው መደብ

2.1 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ **የአስተዳደርና ተማሪዎች አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት (የስራ ዝርዝሩን ዩኒቨርሲቲው ድረ-ገጽ ይመልከቱ)**

2.2 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ **የተቋማዊ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት (የስራ ዝርዝሩን ዩኒቨርሲቲው ድረ-ገጽ ይመልከቱ)**

## 3. የማመልከቻ መስፈርቶች

3.1 **የማመልከቻ ደብዳቤ፡-** ከአንድ ገጽ ያልበለጠ ለሚያመለክቱበት የኃላፊነት ቦታ ያመለከቱበትን ምክንያት የሚገልጽ ማመልከቻ

3.2 **የትምህርት ደረጃ፡-** ሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ወይም ሁለተኛ ዲግሪ ( MA/MSc) እና ቢያንስ የረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ያለው/ያላት

3.3 **የሥራ ልምድ:-** በከፍተኛ ትምህርት፣ በምርምር ተቋማት ወይም መሰል ተልዕኮ ባላቸው ተቋማት በአመራር ወይም በኃላፊነት እርከን የተረጋገጠ ልምድ ያለው/ያላት፣

3.4 **አጭር ፕሮፖዛል ማቅረብ:-** አመልካቾች የሚወዳደሩበትን ዘርፍ በዋና ተግባር ለማሳደግና ለማሻሻል ስለሚከተሉት ስልቶች ከ5 ገጽ ያልበለጠ ፕሮፖዛል በእንግሊዝኛ ቋንቋ በፅሑፍ ያቀርባሉ፤ ባቀረቡት ፕሮፖዛል ላይ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ገለፃ ያደርጋሉ፤

3.5 **ፆታ:-** ማስታወቂያው ወንዶችንና ሴቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን መስፈርቱን የሚያሟሉ ሴቶች ሁሉ እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ፤

3.6 **እድሜ** ከ65 ዓመት ያልበለጠ/ያልበለጠች

## 4. ተፈላጊ ክህሎቶች:-

4.1 **የአመራር ክህሎት :-** አመልካቾች በሚወዳደሩበት ስራ መደብ ያለውን የሰው፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ሃብት በማስተባበር፣ ለመምራት የሚያስችል ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው፣

4.2 **አዲስ አሰራር የመፍጠርና ለውጥ የማምጣት ክህሎት:-** አመልካቾች በሚወዳደሩበት ስራ መደብ ለውጥና እድገትን ለማምጣት የሚያስችሉ አዳዲስ የአሰራር ስልቶችን የማመንጨትና ተግባራዊ የማድረግ አቅም ያላቸው መሆን አለባቸው፤

4.3 **የተግባቦት ክህሎት:-** አመልካቾች የስራ ዘርፋቸውንም ሆነ የዩኒቨርሲቲውን ተልዕኮና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችል የተግባቦት ክህሎት ያላቸው መሆን አለባቸው፣

## 5. ተፈላጊ ሥነ-ምግባራዊ ባህርያት

5.1 አመልካቾች ከስነ-ምግባር ጉድለቶች የፀዱ፣ በመልካም ባህርያቸውና በስራ አክባሪነታቸውና ታታሪነታቸው የተመሰከረላቸውና ለሌሎች አርአያነታቸው የጎላ መሆን አለባቸው

5.2 አመልካቾች ተግባብቶ የመስራት፣ ሁሉን በእኩል የማስተናገድ፣ ለሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ በተገቢው ጊዜ የመስጠት መርህ የሚከተሉ መሆን አለባቸው

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ Federal ... Republic of Ethiopia ... ity